# <u>የስድስተኛ ክፍል አማርኛ የሞዴል ፈተና መለማመጃ</u>

## <u>ጥያቄ አንድ</u>

### <u>ምንባብ</u>

ፉንጋይ ብላችሁ ልትጠሩኝ ትችላላችሁ። በሕይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ያወኳቸው እናትና አባቴን ነበር። የአባቴ ቁመና እና መልክ አሁንም ትውስ ይለኛል። ዜራም ኢንቻ ጠይም፣ አጭርና ወፍራም ነበር። አዘውትሮ የሚለብሰው ሹራብና ቁምጣ ሲሆን ብዙውን ግዜ ሰንደል ጫማ ይጫማ ነበር።

በሰንበት ቀናት ነጭ በንጭ ተፈሪ ቅድ ጠባብ ሱሬውን ይታጠቅና ከላይ ረጅም ቀሚስና ሹራብ ለብሶ ባላዩ ላይ ሳሪያን ኮቱን ይደርብበታል። ስድስት ባትሪ ጎራሽ ሬዲዮም ነበረን። ይህንን ሬዲዮናችንን ዳንቴል ያለብስና አንግቶት እስከመጨረሻው ከፍቶት ይንሸራሸራል። እኔንም የከት ልብሴን አልብሶን በሚንሸራሸርበት ሁሉ ያስከትለኝ ነበር። ሬዲዮናችን ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ እያንፀባረቀ ዕቁብ ወደሚጥልበት አጎራባች ቤት ተያይዘን እንሄዳለን። ብዙም ሳንቆይ ሬዲዮናችን የዕለቱን ዜና እወጃ መጀመሩን ያበስረናል።

<< እንደምን ዋላችሁ ዜና እናሰማለን። ዜናውን የማሰማችሁ አሳምነው ገብረወልድ >> ነኝ ሲል ጋዜጠኛው ጆሮ ገብ በሆነ ድምፅ የታዳሚውን ቀልብ ይገዛል። ከ እቁብተኞቹ አንዳንዶቹ << ዛሄር ይመስገን>> በማለት ለሬድዮናችን እጅ እየነሱ ምላሽ ይሰጣሉ። ሁሉም ታዳሚዎች ዜናውን ለማድመጥ በአድናቆት ያቆበቁባሉ።

በምንባቡ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ስጡ

1. ምንባቡ ስንት አንቀጽ ያለው ነው?

   ሀ) አራት ለ) ስድስት ሐ) ሶስት መ) አንድ

2. አሁንም **<u>ትውስ</u>** ይለኛል ሲል ምን ማለቱ ነው?

   ሀ) ቅር ይለኛል ለ) ትዝ ይለኛል ሐ) ይናፍቀኛል መ) ይረሳኛል

3. ሰንደል ጫማ **<u>ይጫማ</u>** ነበር ። የተሰመረበት ቃል ትርጓሜ

   ሀ) ይገዛ ለ) ያጠልቅ ሐ) ይለብስ መ) ያመጣ

LIVEWORKSHEETS

4. ዳንቴል ያለብስና **<u>እንግቶት</u>** እስከመጨረሻው ከፍቶት ይንሸራሸራል። የተሰመረበት ቃል ትርጓሜ

ሀ) ተሸከሞት ለ) አዝሎት ሐ) ትከሻው ላይ አንተልጥሎት

5. የክት ልብሴን ሲል፡

ሀ) የታጠበ ልብስ ለ) አዲስ ልብስ

ሐ) ለተለየ ቀን ብቻ የሚለበስ ልብስ መ) የተትኮሰ ልብስ

6. **<u>ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ</u>** ማለት ምን ማለት ነው ?

ሀ) ከቅርብ እስከ ሩቅ ለ) ከጥግ እስከ ጥግ

ሐ) ከመሬት እስከ ሰማይ መ) ከቤት እስከ ጎረቤት

7. ጋዜጠኛው **<u>ጆሮ ገብ</u>** በሆነ ድምፅ ሲል

ሀ) ለጆሮ የሚከብድ ለ) ለመስማት የሚጋብዝ

ሐ) ጮክ ያለ ድምጽ መ) ለስላሳ ድምጽ

8. የታዳሚውን **<u>ቀልብ</u>** ይገዛል። የተሰመረበት ቃል ትርጓሜ

ሀ) ትኩረት ይስባል ለ) ልብ ይሰርቃል

ሐ) አይን መ) ሀ እና ለ

**9. <u>እጅ እየነሱ</u>** ሲል

ሀ) እጅ እያወጡ ለ) አክብሮት እያሳዩ

ሐ) እጅ እየሰበሰቡ መ) እጃቸውን እያጠፉ

10. በአድናቆት **<u>ያቆበቁባሉ</u>**

ሀ) ዜናውን ለመስማት ይጓጓሉ ለ) ዜናውን ለመስማት ይቸኩላሉ

ሐ) ለመሄድ ይቸኩላሉ መ) ሀ እና ለ

LIVEWORKSHEETS

## ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ

11. ገበያተኛው ነፍስ ዘርቶ **መላወስ** ጀምሯል ሲል

ሀ) መተንፈስ ለ) መነጋገር ሐ) መንቀሳቀስ መ) ማስተዋል

12. ሁሉም **በየፈናው** ወዲያ ወዲህ ይርመሰመሳል ሲል

ሀ) ሁሉም በየ አቅጣጫው ይሯሯጣል ለ) ሁሉም በሚፈልገው መንገድ ይንቀሳቀሳል

ሐ) ሁሉም በያለበት ተቀምጧል መ) ሀ እና ለ

13. ገበያው **ረጭ** ብሎ ዋለ

ሀ) ሞቅ ብሎ ለ) ፀጥ ብሎ ዋለ ሐ) ሲረበሽ ዋለ መ) ሲተራመስ ዋለ

14. ከተለያዩ ምንጮች መረጃ ለማኘት የምንጠቀምባቸው ክሂሎች ከሚከተሉት መካከል የትኞቹ ናቸው ?

ሀ) መፃፍና መናገር ለ) ማንበብና ማዳመጥ

ሐ) ማንበብና መናገር መ) መፃፍና ማንበብ

15. እዕሱን ተመርኩዞ ( ተንተርሶ ) ዝርዝር ሃሳቦች የሚቀርቡበት የድርሰት ክፍል ምን ይባላል?

ሀ) ሀተታ ለ) ርዕስ ሐ) መግቢያ መ) መደምደሚያ

16. ከሚከተሉት ቢቃላዊ ግጥሞች ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው ?

ሀ) ሙሾ ለ) ቀረርቶ

ሐ) ፉከራ መ) ተረት

17. ከሚከተሉት ውስጥ **ተግዳሮት** ለሚለው ቃል፣ተመሳሳይ የሆነው የቱ ነው?

ሀ) አረጀ ለ) ደከመ ሐ) ችግር መ) ምቾት

18. **ህቡዕ** ለሚለው ቃልተቃራኒ የሆነው የቱ ነው?

ሀ) ስውር ለ) ድብቅ ሐ) ገሃድ መ) ይማይታይ

19. የጊዜ ግሶች የሚባሉት እነማን ናቸው?

ሀ) የወደፊት ጊዜ ለ) የአሁን ጊዜ ሐ) የሃላፊ ጊዜ

መ) የትንቢት ጊዜ ሠ) ሁሉም

20. ከሚከተሉት መካከል ልዩ የሆነው የቱ ነው?

ሀ) ኩራዝ ለ) ጉቶ ሐ) ገንቦ መ) አውራ

LIVEWORKSHEETS

21. **<u>ወሰፌ</u>** የሚለው ቃል በቃል ከሚሰጠው ትርጉም የተለየ ገብቶ የሚገኘው የቱ ላይ ነው?

ሀ) መስፈያ ለ) ቀጭን ሐ) ተንኮለኛ መ) ሆዳም

22. **<u>እሳት</u>** የሚለው ቃል ከሚሰጠው ትርጉም የተለየ ገብቶ የሚገኘው ይርቱ ላይ ነው?

ሀ) ልጅቱ በእሳት ትጫወታለች ለ) ልጂቱ እሳት ጫረች

ሐ) ልጂቱ እሳት ናት መ) የእሳት ፍንጣሪ አቃጠላት

23. **<u>መፅሀፌ</u>** በሚለው ቃል ውስጥ ያለው ቅጥያ ሙያው ምንን መግለፅ ነው?

ሀ) ባለቤትን ለ) ተሳቢን ሐ) ባለንብረትነትን መ) ግስን

24. **<u>መስህቦቻችን</u>** የሚለው ቃል በም ዕላድ ተነጣጥሎ ሲፃፍ ትክክለኛ የቱ ነው?

ሀ) መስህብ -ኦቻችን ለ) መስህብ- ኦ- ቻችን

ሐ) መስህብ- ኦች- ኦችን መ) መስህብ- ቦቻችን

25. የእሷን **<u>ኩብሪትነት</u>** ብዙ ሰዎች ተረድተዋል፡፡ የተሰመረበት ቃል ፍካሪያዊ ፍቺ የቱ ነው ?

ሀ) እሳት ለማቀጣጠል ለ) ለመጫር ሐ) ነገር አጫሪነት

መ) ነገር ፈላጊነት ሠ) ሐ እና መ መልሶች ናቸው

26. ከተዘረዘሩት መካከል የአንቀፅ አፃፃፍ ዘዴዎች ከሆኑት መካከል ያልሆነው የቱ ነው ?

ሀ) ተራኪ ለ) ገላጭ ሐ) አመዛዛኝ

መ) ስዕላዊ ሠ) መግቢያ

27. ከተዘረዘሩት ዓለፍተ ነገሮች መካከል ሰዋሰዋዊ ግድፈት ያለበት የትኛው ነው?

ሀ) አስቴር ልጇን ሙያ አስተማረች ለ) ሁኔታ አለፈ በጥሩ ፈተናውን

ሐ) ተወካያቸውን መረጡ የክፍል ተማሪዎች መ) ሁሉም ሠ) ለ እና ሐ መልሶች ናቸው

28. ታናሽ ወንድሜ የተወለደው የዛሬ አስር ዓመት ነበር፡፡

ሀ) የአሁን ጊዜ ለ) የወደፊት ጊዜ ሐ) ሀላፊ ጊዜ መ) የትንቢት ጊዜ

29. የ **<u>ዞግባ</u>** አማሪያዊ ፍቺ.......... ነው

ሀ) በጣም ረጅም የሆነ የዛፍ ዓይነት ለ) አጭር የዛፍ ዓይነት

ሐ) ረጅም ሰው መ) አጭር ሰው

LIVEWORKSHEETS

30. የ **<u>ፍየል</u>** ፍካሪያዊ ፍቺ ........ ነው፡፡

ሀ) ኀበዝ　　ለ) ለፍላፊ　　ሐ) የማያወራ　　መ) ሁሉም

31. **<u>አልጋ</u>** ለሚለው ቃል አማሪያዊ ፍቺ የሚሆነው፡

ሀ) መኘታ　　ለ) ዙፋን　　ሐ) ዘውድ　　መ) ሁሉም

32. **<u>ምስጥ</u>** ለሚለው ቃል ፍካሪያዊ ፍቺ የሚሆነው፡-

ሀ) አጭር　　ለ) ተንኮለኛ　　ሐ) ፈጣን　　መ) ታታሪ

33. ከሚከተሉት ውስጥ የጊዜ ተውሳከ ግስ የሆነው የቱ ነው ?

ሀ) እዚህ　　ለ) ፊትለፊት　　ሐ) ድንገት　　መ) በየቀኑ

34. አበበ **<u>ከፉኛ</u>** ተጎዳ፡፡ የተሰመረበት ተውሳከ ግስ የገባው ከምን አንፃር ነው ?

ሀ) ከቦታ　　ለ) ከሁኔታ　　ሐ) ከቁጥር　　መ) ከጊዜ

35. ከሚከተሉት ውስጥ ለአመዛዛኝ ፅሁፍ ርዕስ ሊሆን እሚችለው የቱ ነው ?

ሀ) የውሃ ጥቅሞች　　ለ) ገጠርና ከተማ

ሐ) የምግብ ዓይነቶች　　መ) ሁሉም

LIVEWORKSHEETS